# ነጋሪት ጋዜጣ ትግራይ

## የትግራይ ነጋሪት ጋዜጣ

ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ

የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

መበል 26 ዓመት ቑ.1 መቐለ 332/2012ዓ/ም

ብሓልዮት ቤት ምኽሪ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ዝወፀ

26ኛ ዓመት ቁ.1 መቐለ 332/2012ዓ/ም


**ኣወዳደባ፣ ስልጣንን ተግባርን ኣብያተ ፍርዲ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ንምውሳን ዝወፀ ቁፅሪ ኣዋጅ 332/2012ዓ.ም.**

ነፃነትን ተሓታትነትን ስርዓት ዳይነት ክልል ትግራይ ብዘተኣማምን ኩነታት ተጠናኺሩ ኣብያተ ፍርዲ ንዝተጣየሻሉ ዕላማን ልኡኹን ክዐውታ ዘኽእለን ዝርዝር ሕጊ ምውፃእ ኣገዳሲ ኮይኑ ብምርካቡ፤

ኣብያተ ፍርዲ ክልል ትግራይ ተበፃሓይ፣ ስሉጥ፣ ፅሩይን ውፅኢታዊ ዝኾነን ግልጋሎት ዳይነት ንምሃብ ዘኽእለንን እቲ ክልል ዝበፀሖ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያውን ማሕበራውን ብርኪ ዕብየት ዝምጥን ስልጣንን አወዳድባን ክህልወን ብምግባር ኣብ ምስፋን ሰላም፣ ልምዓትን ህንፀት ስርዓት ዴሞክራስን ብዕሒተን ንምውፋይ ዘኽእለን ሕጊ ምድንጋግ አድላዪ ኾይኑ ስለዝተረኸበ፤

ስልጣንን ኣሰራርሓን ሰበር ሰማዒ መጋባእያ ክልል ትግራይ ትፅቢት ብዝግበረሉ ደረጃ ውፅኢታውን ግልፅን ክኸውን ብዘኽእሎ ኣገባብ ክመዓራረ ምግባር ኣድላይ ኮይኑ ብምርካቡ፤

**የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የፍርድ ቤቶች ኣደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 332/2012ዓ.ም.**

የትግራይ ክልል የዳኝነት ስርአት ነፃነትና ተጠያቂነት አስተማማኝ በሆነ መልኩ ተጠናክሮ እንዲቀጥልና ፍርድ ቤቶች የተቋቋሙበት ዓላማና ተልእኮ ለማሳካት የሚያስችላቸው ዝርዝር ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የትግራይ ክልል ፍርድ ቤቶች ተደራሽ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የዳኝነት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችላቸው እና ክልሉ በፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ እና ማሕበራዊ ለደረሰበት የእድገት ደረጃ የሚመጥን ስልጣንና አደረጃጀት እንዲኖራቸው በማድረግ ተየበክልሉ ሰላም፣ ልማትና ዴሞክራሲ የድርሻቸውን ኣስተዋፅኦ ለማድረግ የሚያስችላቸው የሕግ ድንጋጌ እንዲኖር ማድረግ በማስፈለጉ፣

የትግራይ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣንና አሰራር ግልፅነት የተላበሰና በሚጠበቀው ደረጃ ውጤታማ እንዲሆን በሚያስችለው መንገድ ለውጦች ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ቤት ምኽሪ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ብመሰረት ተመሓይሹ ዝወፀ ሕገ መንግስቲ ዓንቀፅ 49(3)(ሀ) እዚ ኣዋጅ ኣውፂኡ ኣሎ።

## ክፍሊ ሓደ

## ሓፈሻዊ ድንጋገታት

**ዓንቀፅ1. ሓፂር ርእሲ**

እዚ ኣዋጅ "ኣዋጅ ኣብያተ ፍርዲ ክልል ትግራይ ቁፅሪ-------/2011ዓ.ም." ተባሂሉ ክጥቀስ ይኽእል።

**ዓንቀፅ 2.ትርጉም**

ኣጠቓቕማ እቲ ቃል ካሊእ ትርጉም ዘውህቦ እንተዘይኮይኑ ኣብ ውሽጢ እዚ ኣዋጅ ፡

1. **"ሕገ መንግስቲ"** ማለት ተመሓይሹ ዝወፀ ሕገ መንግስቲ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ እዩ።
2. **"ቤት ምኽሪ"** ማለት ቤት ምኽሪ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ እዩ።
3. **"ቤት ፍርዲ"** ማለት ላዕለዋይ፣ ማእኸላይን ወረዳን ቤት ፍርዲ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ዘጠቓለለ እዩ።
4. **"ፕረዚደንት"** ማለት ፕረዚደንት ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ኮይኑ ከከም ኣጠቓቕማ እቲ ቃል ንፕረዚደንት ማእኸላይ ወይ ወረዳ ቤት ፍርዲ ክውክል ይኽእል ።
5. **"ዳይና"** ማለት ኣብ ቤት ፍርዲ ብዳይነት ተመዲቡ ክሰርሕ ብቤት ምኽሪ ዝተሾመ በዓል ሞያ ሕጊ እዩ።
6. " **ሓጋዚ ዳይና"** ማለት ኣብ ስራሕቲ ዳይነት ዳይና ንምሕጋዝ ዝቑፀር በዓል ሞያ ሕጊ እዩ።

የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተሻሽሎ በወጣው ህገ መንግስት ዓንቀፅ 49(3)(ሀ) መሠረት ይህን አዋጅ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**ዓንቀፅ 1.አጭር ርእስ**

ይህ አዋጅ "የትግራይ ክልል የፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር ----/2011ዓ.ም "ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**ዓንቀፅ 2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ፡

1. **"ሕገ መንግስት"** ማለት ተሻሽሎ የወጣው የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሕገ-መንግስት ነው።
2. **"ምክር ቤት"** ማለት የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ነው።
3. **"ፍርድ ቤት"** ማለት የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ፣ ከፍተኛ እና ወረዳ ፍርድ ቤትን ያጠቃልላል።
4. **"ፕረዚደንት"** ማለት የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕረዚደንት ሆኖ እንደየቃሉ አጠቃቀም የከፍተኛ ወይም የወረዳ ፍርድ ቤት ፕረዚደንቶችንም ሊወክል ይችላል።
5. **"ዳኛ"** ማለት በፍርድ ቤት በዳኝነት ተመደቦ እንዲሰራ በምክር ቤት የተሾመ የሕግ ባለሙያ ነው።
6. **"ረዳት ዳኛ"** ማለት በዳኝነት ሥራ ዳኛን ለማገዝ የሚቀጠር የሕግ ባለሙያ ነው።

7. **"ሬጅስትራር"** ማለት ኣብ ስራሕ ብዘለዉ ሕግታት መሰረት ዝተወሃብዎ ስልጣንን ተግባርን ንምፍፃም ኣብ ቤት ፍርዲ ተመዲቡ ንክሰርሕ ብቤት ምኽሪ ዝተሸወመ በዓልሙያ እዩ።

8. **"ዋና ሬጅስትራር"** ማለት ንክፍሊ ሬጅስትራር ላዕለዋይ፣ ማእኸላይ ወረዳን ብሓላፍነት ዝመርሕን ብላዕለዋይነት ዘተሓባብርን ተሸያሚ ጉባኤ እዩ።

9. **"ሓላፊ ክፍሊ ሬጅስትራር"** ማለት ንሬጅስትራር ማእኸላይን ወረዳን ኣብያተ ፍርዲ ብሓላፍነት ዝመርሕን ብላዕለዋይነት ዘተሓባብርን ተሸያሚ ጉባኤ እዩ።

10. **"ሰራሕተኛ ቤት ፍርዲ"** ማለት ኣብ ስራሕ ዘሎን ዝምልከቶ ኣካል ቀሪፁ ብዘዕደቖ መሓውር መሰረት ዝቑፀርን ሰራሕተኛ ኮይኑ ብሕጊ ሰራሕተኛ መንግስቲ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ዝመሓደር እዩ።

11. **"ምድብ መጋባእያ"** ማለት ስራሕቲ መጋባእያ ዝሳለጠሉ ቤት ፍርዲ ኾይኑ ከም ኣደላይነቱ ሓደ ወይ ካብ ሓደ መጋባእያ ንላዕሊ ዝሓዘ እዩ።

12. **"መተሓባባሪ ምድብ መጋባእያ"** ማለት ኣብ ሓደ ምድብ መጋባእያ ወይ መጋባእያታት ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ንዘለዉ ዳያኑን ሰራሕተኛታት ቤት ፍርድን መተሓባባሪ ኮይኑ ዝሰርሕ ዳይና እዩ።

13. **"ኣካቢ መጋባእያ"** ማለት ሰለስተ ወይ ካብኡ ንላዕሊ ዝኾኑ ዳያኑ ኣብ ዝሰየምሉ መጋባእያ ኣካቢ ኮይኑ ዝሰርሕ ዳይና እዩ።

7. **"ሬጅስትራር"** ማለት በስራ ላይ ባሉ ሕጎች መሰረት የተሰጡትን ስልጣንና ተግባር ለመከወን በፍርድ ቤት በሬጅስትራርነት ተመድቦ እንዲሰራ በምክር ቤት የተሾመ ባለሙያ ነው።

8. **"ዋና ሬጅስትራር"** ማለት የጠቅላይ፣ የከፍተኛና የወረዳ የሬጅስትራር ክፍል እንዲሁም የወረዳ ፍርድ ቤት ሬጅስትራር የሚመራና በበላይነት ሚያስተባብር የጉባኤ ሹመኛ ነው።

9. **"የሬጅስትራር ክፍል ሓላፊ"** ማለት የከፍተኛ እና ወረዳ ፍርድ ቤት የሬጅስትራር ክፍል የሚመራና በበላይነት ሚያስተባብር የጉባኤ ሹመኛ ነው።

10. **"የፍርድ ቤት ሰራተኛ"** ማለት በስራ ላይ ያለና የሚመለከተው አካል ቀርፆ ባፀደቀው መዋቅር መሰረት የሚቀጠር ሰራተኛ ሆኖ በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ሰራተኞች ሕግ የሚተዳደር ነው።

11. **"ምድብ ችሎት"** ማለት የችሎት ስራ የሚከናወንበት ፍርድ ቤት ሆኖ እንዳስፈላጊነቱ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ችሎት የያዘ ነው።

12. **"የምድብ ችሎት አስተባባሪ"** ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ ምድብ ችሎት ያሉት ወይም በጠቅላይ ፍርድ ቤት ላሉ ዳኞችና ሰራተኞች አስተባባሪ ሆኖ የሚሰራ ዳኛ ነው።

13. **"የችሎት ሰብሳቢ"** ማለት ሶስት ወይም ከሶስት በላይ የሆኑ ዳኞች በሚሰየሙበት ችሎት ሰብሳቢ ሆኖ የሚሰራ ዳኛ ነዉ።

14 "**ዝተለወጠ ውሳነ**" ማለት ይግብኣኒ ሰማዒ ቤት ፍርዲ ብትሕቲኡ ዘሎ ቤት ፍርዲ ንዝሃቦ ትእዛዝ፣ ብይን፣ፍርዲ ወይ ውሳነ ሙሉእ ብሙሉእ ካብ ምፅናዕ ወፃኢ ዝገብሮ ዝኾነ ዓይነት ለውጢ ይሓውስ።

15. "**በዓል መዚ**" ማለት ናይዚ ክልል ኣፈ ጉባኤን ምክትል ኣፈ ጉባኤን ቤት ምኽሪ፣ ኣባለት ቀዋሚ ኮሚቴ ቤት ምኽሪ፣ ፕሬዚዳንትን ምክትል ፕሬዝዳንትን ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ፣ ዳያኑ ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ፣ ሓለፍቲ ቢሮታት ካብ ደረጃ ሓላፊ ቢሮ ንላዕሊ ዝኾኑ ሰብ መዚ መንግስቲ፣ ምክትል ሓለፍቲ ቢሮ፣ ዋና ኦዲተርን ምክትል ዋና ኦዲተርን፣ ኮሚሽነራትን ምክትል ኮሚሽነራትን፣ ሓለፍቲ ቤት ፅሕፈትን ኤጀንስን፣ ዋና ኣማሓዳሪ ዞባ፣ ምክትል ዋና ኣማሓዳሪ ዞባ፣ ኣፈፀምቲ ስራሕ ዞባ፣ ፕሬዚዳንትን ምክትል ፕረዚደንትን ማእኸላይ ቤት ፍርዲ፣ ዳያኑ ማእኸላይ ቤት ፍርዲ፣ ሓለፍቲ ኣብያተ ዕዮ ዞባ፣ ዋና ኣማሓዳሪ ወረዳ፣ ፕሬዚዳንት ወረዳ ቤት ፍርዲ፣ ዳይና ወረዳ ቤት ፍርዲ፣ ሓለፍቲ ቤት ፅሕፈት ወረዳን ልዕል ኢሎም ምስ ዝተገለፁ ተመሳሳሊ መዝነት ዘለዎም ኣካላትን የጠቓልል።

16." ክልል" ማለት ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ እዩ።

17. "ዋኒን ክልል" ማለት ኣብዚ ክልል ብውክልና ብላዕለዋይ ወይ ማእኸላይ ቤትፍርዲ ካብ ዝርኣዩ ዋኒናት ፌደራል ወፃኢ ዝኾኑ ኩሎም ዋኒናት ዘጠቓለለ እዩ።

18."**ጉባኤ**" ማለት ጉባኤ ምምሕዳር ዳያኑ ብሄራዊ

14. "**የተለወጠ ውሳኔ**" ማለት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የበታች ፍርድ ቤት የሰጠውን ትእዛዝ፣ ብይን፣ ፍርድ ወይም ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ከማፅናት ውጪ የሚያደርገው ማንኛውም ዓይነት ለውጥ ያጠቃልላል።

15. **ባለ-ስልጣን**" ማለት የክልሉ የምክር ቤት አፈ ጉባኤና ምክትል አፈ ጉባኤ፣ የምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ የቢሮ ሃላፊዎችና ከቢሮ ሃላፊ ደረጃ በላይ የሆኑ የመንግስት ባለስልጣኖች፣ ምክትል የቢሮ ሃላፊዎች፣ ዋና ኦዲተር እና ምክትል ዋና ኦዲተር፣ ኮሚሽነሮችን እና ምክትል ኮሚሽነሮች፣ የፅህፈት ቤትና ኤጀንሲ ሃላፊዎች፣ የዞን ዋና አስተዳዳሪ፣ ምክትል የዞን አስተዳዳሪ፣ የዞን ስራ አስፈፃሚዎች፣ የዞን ፅህፈት ቤት ሃላፊዎች፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕረዚደንት፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ፣ የወረዳ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ የወረዳ ፅህፈት ቤት ሃላፊዎችና ከላይ ከተገለፁት ጋር ተመሳሳይ ስልጣን ያላቸው አካላትን ያጠቃልላል።

16."ክልል" ማለት የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ነው።

17. "የክልል ጉዳይ" ማለት በክልሉ ጠቅላይ ወይም ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውክልና ከሚታዩ የፌደራል ጉዳዮች ዉጭ የሆኑትን ሁሉም ጉዳዮች የሚያጠቃልል ነዉ።

18."**ጉባኤ**" ማለት የትግራይ ብሄራዊ ክልልዊ

ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ እዩ።

19."ሰብ" ማለት ናይ ተፈጥሮ ሰብ ወይ ብሕጊ መሰል ሰብነት ዝተወሃቦ ኣካል እዩ።

**ዓንቀፅ 3. ወሰን ተፈፃምነት**

ተፈፃምነት እዚ ኣዋጅ፡-

1. ኣብ ልዕሊ ወረዳ፣ ማእኸላይን ላዕለዋይን ቤት ፍርዲ፣
2. ኣብ ልዕሊ ክልላዊ ዋኒን፣
3. ኣብ ልዕሊ ብውክልና ዝርአ ፌደራል ዋኒን ይኸውን።

**ዓንቀፅ 4.ኣገላልፃ ፆታ**

ኣብዚ ኣዋጅ ብተባዕታይ ፆታ ዝተደንገገ ንኣንስተይቲ ፆታ 'ዉን ዝሓውስ እዩ።

**ዓንቀፅ 5. ቋንቋ ስራሕ**

1. ቋንቋ ስራሕ ቤት ፍርዲ ትግርኛ እዩ።
2. ቋንቋ ትግርኛ ንዘይኽእል ብገበን ዝተኸሰሰ ሰብ ወይ ምስክር ቤት ፍርዲ ተርጓሚ ክምደበሉ ይገብር።
3. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 2 እንተሃለወ'ውን ቋንቋ ትግርኛ ዘይኽእል ወዳኢ ነገር ወይ ወኪል ቤት ዕዮ ወይ ጠበቓ ቆፂሩ ዝቐርብ ተኸሳሲ ገበን ተርጓሚ ባዕሉ የቕርብ።

**ዓንቀፅ 6.መሰል ምርካብ ግልጋሎት ተኸላኻሊ ጠበቓ**

ብገበን ዝተኸሰሰ ሰብ ግልጋሎት ተኸላኻሊ ጠበቓ ይገበረለይ ኢሉ እንተሓተተ፤ ዓቕሚ ዘይብሉ ምዃኑ መረዳእታ እንተቕርብን ተመርሚሩ ዓቕሚ ዘይብሉ ምዃኑ እንተረጋገፅን ተኸሳሲ ብዘይጠበቓ እንተተኸራኺሩ ፍትሒ ክጓደል ይኽእል እዩ ኢሉ ቤት ፍርዲ እንተኣሚኑ ብመንግስቲ ተኸላኻሊ ጠበቓ ክምድበሉ ወይ

መንግስት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ነዉ።

19"ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠዉ አካል ነው።

**ዓንቀፅ 3. የተፈፃሚነት ወሰን**

የዚህ አዋጅ ተፈፃሚነት፡-

1. በወረዳ፣ ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ላይ፣
2. በክልል ጉዳይ ላይ፣
3. በውክልና በሚታይ የፌዴራል ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነትይኖረዋል።

**ዓንቀፅ 4. የፆታ አገላለፅ**

በዚህ አዋጅ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

**ዓንቀፅ 5. የስራ ቋንቋ**

1. የፍርድ ቤት የሥራ ቋንቋ ትግርኛ ነው።
2. ትግርኛ ቋንቋ ለማይችል በወንጀል የተከሰሰን ሰው ወይም ምስክር ፍርድ ቤት ተርጓሚ እንዲመደብለት ያደርጋል።
3. በዚህ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 2 የተደነገገው ቢኖርም ትግርኛ ቋንቋ የማይችል ነገረ ፈጅ ወይም የመስሪያ ቤት ወኪል ወይም ጠበቃ ቀጥሮ የሚቀርብ የወንጀል ተከሳሽ ተርጓሚ ራሱ ያቀርባል።

**ዓንቀፅ 6. የተከላካይ ጠበቃ አገልግሎት የማግኘት መብት**

በወንጀል የተከሰሰ ሰው ተከላካይ ጠበቃ እንዲመደብለት ጥያቄ ሲያቀርብ፤ አቅም የሌለው መሆኑን ማስረጃ ሲያቀርብ እና ተመርምሮ ዓቅም የሌለው መሆኑን ሲረጋገጥና ያለ ጠበቃ ቢከራከር ፍትህ ሊጓደል ይችላል ብሎ ፍርድ ቤቱ ሲያምን በመንግስት ተከላካይ ጠበቃ እንዲመደብለት ወይም በነፃ የሕግ ድጋፍ

ብነፃ ናይ ሕጊ ድጋፍ ክሕገዝ ክገብር ይኽእል።

**ዓንቀፅ 7. ከይዲ መጋባእያ**

1. ቤት ፍርዲ ዝርእዮ ዋኒን ኣብ ግልፂ መጋባእያ ይካየድ።

2. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝተደንገገ እንተሃለወ'ውን ንስራሕቲ ዳይነት ኣግባብነት ዘለዎም ስነ ስርዓት ሕግታት ከምዘለዉ ኮይኖም ንሓለዋ ድሕንነት፣ ፀጥታን ሰላምን ሃገር ኣድላይ ኾይኑ እንትርከብ ወይ ሞራል ህዝቢ፣ ድሕንነት ሰብ ዋኒን ምስክርን ወይ 'ዉን ምሽጢር ቤተሰብ ምሕላው ኣድላይ ኮይኑ እንትርከብ ብዕፅው መጋባእያ ይርአ።

**ዓንቀፅ 8. ዋኒናት ዝምርሕሉ ስርዓት**

1. ኣብዚ ኣዋጅ ዝተደንገገ ሕልው ኮይኑ ንቀጥታን ይግብኣንን ዋኒናት ኣብ ሕጊ ስነ-ስርዓት ገበንን ፍትሃብሄርን ወይ ኣብ ካልኦት ሕግታት ዝተደንገገ ኣካይዳ ተፈፃምነት ይህልዎ።

2. ናብ ሰበር ሰማዒ መጋባእያ ዝቐርብ ጥርዓን ኣብዚ ኣዋጅ ብዝተደንገጉ ሕግታት ስነ-ስርዓትን ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ብዘውፅኦ መምርሒ ስነ-ስርዓትን ይምራሕ።

3. ኣብ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 2 ዝተደንገገ ከምዘሎ ኾይኑ በዚ ኣዋጅን ስዒቡ ብዝወፅእ መምርሒ ስነ-ስርዓት ሰበር ኣብ ዘይተሸፈነ ስነስርዓታዊ ኣካይዳ እቲ ሰበር ሰማዒ መጋባእያ ድንጋገታት ሕጊ ስነ ስርዓት ገበንን ፍትሃብሄርን ወይ ካልኦት ሕግታትን ክኽተል ይኽእል።

**ዓንቀፅ 9. ዳያኑ ካብ መጋባእያ ዝለዓልሉ ኩነታት**

1. ዝኾነ ዳይና ካብዞም ዝስዕቡ ምኽንያታት

እንዲታገዝ ሊያደርግ ይችላል።

**ዓንቀፅ 7. የችሎት አካሄድ**

1.ፍርዲ ቤት የሚያየው ጉዳይ በግልፅ ችሎት ይካሄዳል።

2. በዚህ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም ለዳኝነት አሰራር አግባብነት ያላቸው የስነ-ስርአት ህጎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የሃገር ደህንነት፣ ሰላምና ፀጥታ ለመጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወይም የህዝብ ሞራል፣ የባለጉዳዮች ወይም ምስክር ደህንነት እንዲሁም የቤተሰብ ምስጢር ለመጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በዝግ ችሎት ይታያል።

**ዓንቀፅ 8. ጉዳዮች የሚመሩበት ስርዓት**

1. በዚህ አዋጅ የተደነገገውን እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀልና በፍትሃብሄር ስነ-ስርአት ህግ ወይም በሌሎች ሕጎች የተደነገገው አካሄድ ለቀጥታና ይግባኝ ጉዳዮች ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

2. ለሰበር ችሎት የሚቀርብ አቤቱታ በዚህ አዋጅ በተደነገጉ የስነ ስርዓት ሕጎች እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በሚያወጣው የስነ ስርዓት መመርያ ይመራል።

3. የዚህ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 2 የተደነገገው እንዳለ ሆኖ በዚህ አዋጅና ቀጥሎ በሚወጣው የሰበር ስነ ስርአት መመርያ በማይሸፈን የስነ ስርአት አካሄድ ሰበር ሰሚ ችሎቱ የወንጀል እና የፍትሃብሄር ስነ ስርአት ሕጎች ወይ ሌሎች ሕጎች ሊከተል ይችላል።

**ዓንቀፅ 9. ዳኞች ከችሎት የሚነሱበት ሁኔታ**

1.ማንኛውም ዳኛ ቀጥለው ካሉት ምክንያቶች

ብሓዲኡ ካብ መጋባእያ ክልዓል ይኽእል።

ሀ. እቲ ዳይና ካብቶም ተኻታዕቲ ወገናት ምስ ሓዲኦም ወይ ምስ ክልቲኦም፣ ምስ ጠበቓኦም ወይ ወኪሎም ክሳብ ሓምሻይ ብርኪ ዝበፅሕ ናይ ስጋ ወይ ድማ ክሳብ ሳልሳይ ብርኪ ዝበፅሕ ናይ መውስቦ ዝምድና ዘለዎ እንትኾይኑ ፤ ወይ

ለ. ናይ ሓዲኦም ተኻታዕቲ ወገናት ሞግዚት ወይ ሕጋዊ ወኪል ኣብ ዝኾነሉ ፣ ወዳኢ ነገር፣ ዓቃቢ ሕጊ ወይ ጠበቓ ኣብ ዝነበረሉ እዋን ሒዝዎ ዝነበረ ዋኒን ዝምልከት ክትዕ እንተኾይኑ፤ ወይ

ሐ. ነቲ ዘካትዕ ዋኒን ኣቐዲሙ ብዳይነት ወይ ብዕርቂ ዝረኣዮ ወይ ብዝኾነ መልክዕ ኣብቲ ዋኒን ተጠቃማይ እንተኾይኑ ፤ወይ

መ. ካብቶም ተኻታዕቲ ወገናት ምስ ሓዲኦም ወይ ምስ ጠበቓኦም ኣብ ስሩዕ ቤት ፍርዲ ወይ ናይ ምድናይ ስልጣን ኣብ ዝተወሃቦ ካልእ ኣካል ክትዕ እንተሃልይዎ ፤ወይ

ረ. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 (ሀ-መ) ካብ ዝተቐመጡ ወፃኢ ትኽክለኛ ፍትሒ ከውህብ ኣይኽእልን ዘብሎ ካሊእ ብቑዕ ምኽንያት እንተሃልዩ እዩ።

ሰ. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1(መ) ዝተደንገገ እንተሃለወ 'ውን ብጉድለት ስነምግባር ዝተኸሰሰ ዳይና መሰረት ብምግባር ዝቐረበ ሕቶ ዳይና ይለዓለለይ ናብ ዝምልከቶ ፕረዚደንት ቤት ፍርዲ ቀሪቡ ብይን ይወሃቦ።

2. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝተደንገጉ ምህላዎም እንተፈሊጡ ወይ እንተኣረጋጊፁ እቲ ዳይና ካብ መጋባእያ ተላዒሉ ኣብ ክንድኡ ካሊእ ዳይና ይትካእ።

በአንዱ ከችሎት ሊነሳ ይችላል።

ሀ. ዳኛው በአንደኛው ተከራካሪ ወገን ወይም ከሁለቱም ወይም ከጠበቃው ጋር እስከ አምስተኛ ደረጃ የሚደርስ የስጋ ወይም እስከ ሶስተኛ ደረጃ የሚደርስ የጋብቻ ዝምድና ያለው ሲሆን ፤ወይም

ለ. የአንደኛው ተከራካሪ ወገን ሞግዚት ወይም ሕጋዊ ወኪል በሆነበት ወይም ነገረፈጅ፣ አቃቢ ህግ ወይም ጠበቃ በነበረበት ጊዜ ይዞት የነበረ ጉዳይ የሚመለከት ክርክር ከሆነ ፤ወይም

ሐ. አካራካሪውን ጉዳይ አስቀድሞ በዳኝነት ወይም በእርቅ ያየው ወይም የሚያውቀው ወይም በማንኛዉም ሁኔታ በጉዳዩ ተጠቃሚ ከሆነ ፤ወይም

መ. ከአንደኛው ተከራካሪ ወገን ወይም ከጠበቃው ጋር በመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም ለመዳኘት ስልጣን በተሰጠው ሌላ አካል ክርክር ካለበት ፣ወይም

ረ. በዚህ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ከፊደል (ሀ-መ) ከተጠቀሰሱት ውጭ ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት አያስችልም የሚያሰኝ ሌላ በቂ ምክንያት ያለ እንደሆነ ነው።

ሰ. በዚህ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1(መ) የተደነገገው ቢኖርም በስነ ምግባር ግድፈት የተከሰሰ ዳኛ በመሆኑ ከችሎቱ ይነሳልኝ የሚል ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ ለሚመለከተው የፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ቀርቦ ብይን ይሰጥበታል።

2. በዚህ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 የተደነገጉት መኖራቸውን ካወቀ ወይም ካረጋገጠ ዳኛው ከችሎቱ ተነስቶ በምትኩ ሌላ ዳኛ ይተካል።

3. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 (ሐ) ዝተደንገገ እንተሃለወ `ኳ መዝገብ ተኸፊቱ ናብ ዳይና ምስቀረበ ንመጀመሪያ ጊዜ ዝወሃብ ትእዛዝ፣ ተለዋጢ ቆፀሮ ምሃብ፣ ምስማዕን ምእዛዝን ዋኒን ኣፈፃፅማ፣ ኣብ ሕቶ ዉሕስና ዉሳነ ምሃብ፣ ብይግባኣኒ ሰማዒ ዝወሃብ ትእዛዝ ሕልው ኮይኑ ብነጥቢ ዝተመለሰ ዋኒን ፍትሃብሄር ዝኣመሰሉ ብምርኣዩ ኣቐዲሙ ብዳይነት ከምዝረኣዮ ኣየቑፅሮን።

**ዓንቀፅ 10. <u>ዳይና ካብ መጋባእያ ንኽለዓል ዝቐርብ ጥርዓን</u>**

1. ኣብዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 9 ብዝተዘርዘሩ ምኽንያታት ሓደ ዳይና ካብ መጋባእያ ክለዓል ዝግብኦ መሲሉ ዝተርኣዮ ተኻታዒ ወገን እቲ ዳይና ንክለዓለሉ ነቲ መጋባእያ ብፅሑፍ ከመልክት ይኽእል።

2. መመልከቲ ጥርዓን ዝቐርብ ቅድሚ ፍርዲ ንምቅዋም ዘኽእል ብቑዕ ምኽንያት ምህላዉ ኣመልካቲ ኣብ ዝፈለጠሉ እዋን ሽዑ ንሽዑ ይኸውን።

3. ካብቲ መጋባእያ ንክለዓል ጥርዓን ዝቐረቦ ዳይና፦

ሀ. ኣብዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 9 ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝተዘርዘሩ መልዐልቲ ምኽንያታት ሓዲኦም ምህልዎም እንተረጋጊፁ ካብ መጋባእያ ይለዓል

ለ. ነቲ ሕቶ ዘይተቐበሎ እንተኾይኑ ኣብቲ ቤት ፍርዲ ብዝርከብ ካሊእ መጋባእያ ወይ ብኻልኦት ዳያኑ ነቲ ዋኒን ንከይሪኦ ብቑዕ ምኽንያት ምህላዉ ወይ ዘይምህላዉ ብይን ይወሃቦ።

ሐ. እቲ መጋባእያ ሓደ ዳይና ጥራሕ

3. በዚህ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 (ሐ) የተደነገገ ቢኖርም መዝገብ ተከፍቶ ለዳኛ ከቀረበ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚሰጥ ትእዛዝ፣ ተለዋጭ ቀን ቀጠሮ መስጠት፤ የፍርድ አፈፃፀም ጉዳይ መስማት እና ማዘዝ፤ በዋስትና ጥያቄ ላይ ውሳኔ መስጠት፤ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሚሰጥ ትእዛዝ እንደተጠበቀ ሆኖ በነጥብ በተመለሰ የፍትሃብሄር ጉዳይ የመሳሰሉትን በማየቱ አስቀድሞ በዳኝነት እንዳየው አያስቆጥረውም።

**ዓንቀፅ 10. <u>ዳኛ ከችሎቱ እንዲነሳ የሚቀርብ አቤቱታ</u>**

1. በዚህ አዋጅ ዓንቀፅ 9 በተዘረዘሩት ምክንያቶች አንድ ዳኛ ከችሎቱ መነሳት የሚገባው መስሎ የታየው ተከራካሪ ወገን ዳኛው እንዲነሳለት ለችሎቱ ምክንያቱን ገልፆ ማመልከቻ በፅሑፍ ማቅረብ ይችላል።

2. የአቤቱታ ማመልከቻ መቅረብ የሚችለው ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ለመቃወም የሚያስችል በቂ ምክንያት መኖሩን ኣመልካች ባወቀበት ጊዜ ወዲያውኑ ይሆናል።

3. ከችሎት እንዲነሳ አቤቱታ የቀረበበት ዳኛ፡-

ሀ. በዚህ አዋጅ በዓንቀፅ 9 ንኡስ ዓንቀፅ 1የተዘረዘሩትን ከችሎት የሚነሳባቸው ምክንያቶች መኖራቸው ካረጋገጠ ከችሎቱ ይነሳል።

ለ. ጥያቄውን ያልተቀበለው እንደሆነ በፍርድ ቤቱ ውስጥ በሚገኝ ሌላ ችሎት ወይም በሌሎች ዳኞች ጉዳዩን ላለማየት በቂ ምክንያት መኖሩን ወይም አለመኖሩን ብይን ይሰጥበታል።

ሐ. ችሎቱ አንድ ዳኛ ብቻ የተሰየመበት

ዝተሰየመሉ እንተኾይኑን ካልኦት ዳያኑ እንተዘይሃልዮምን እቲ ጥርዓን ናብ ዝምልከቶ ፕረዝደንት ቤት ፍርዲ ቀሪቡ ብይን ይወሃቦ።

መ. ካብ መጋባእያ ክለዓል ጥርዓን ዝቐረቦ ዳይና ዝተሰየመሉ መጋባእያ ሰለስተን ልዕሊኡን ዝተሰየምሉ እንተኾይኑ እቲ ጥርዓን በቶም ዝተረፉ ዳያኑን ከምኡ'ውን ፕረዚደንት ወይ መተሓባበሪ እቲ ቤት ፍርዲ ብዘለወሉ ይውሰን።

ረ. ጥርዓን ዝቐረቦ ዳይና ነቲ ዋኒን ንክይሪኦ ብይን እንተተዋሂቡ ብካሊእ ዳይና ወይ ብካልኦት ዳያኑ ክርአ ይግበር።

4 ብመሰረት እዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 3 (ለ)፣ (ሐ)ን (መ)ን ዝወሃብ ብይን እቲ መመልከቲ ካብ ዝቐረበሉ አብ ውሽጢ ዓሰርተ ሓሙሽተ(15) መዓልቲ ክውሰን ዝግባእ ኾይኑ እቲ ውሳነ ናይ መወዳእታን ይግባኣኒ ዘይበሃሎን ይኸውን።

## ዓንቀፅ11. ጥርዓን ዘስዕቦ ኪሳራ

ብመሰረት እዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 10 ዳይና ካብ መጋባእያ ንክለዓል ጥርዓን ቀሪቡ ብቤት ፍርዲ ተቀባልነት ከይረኸበ ብምትራፉ አብ ልዕሊ እቲ ሓደ ተኸራኻሪ ወገን ዘስዕቦ ኪሳራ እንተሃልዩ ሽዑ ንሽዑ ወይ ምስ ናይቲ ዋና ጉዳይ ኪሳራ ተጠቓሊሉ ክውሰን ይኽእል።

## ክፍሊ ክልተ
## ኣወዳድባ ቤት ፍርዲ

## ዓንቀፅ 12. ብርኪታት ቤት ፍርዲ

1. ቤት ፍርዲ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ብሕገ መንግስቲ ክልልና ከምዝተደንገገ ከከም ብርኪ ስልጣኖም ካብ ላዕሊ ናብ ታሕቲ እንትስርዑ፤

እንደሆነና ሌሎች ዳኞች ከሌሉ ጉዳዩ ለሚመለከተው የፍርድ ቤቱ ፕረዝዳንት ቀርቦ ብይን ይሰጥበታል፣ ።

መ. ከችሎቱ እንዲነሳ አቤቱታ የቀረበበት ዳኛ የተሰየመበት ችሎት ሶስት ወይም ከዛ በላይ ዳኞች የሚሰየሙበት ሲሆን አቤቱታው በተቀሩት ዳኞች እንዲሁም ፕሬዝደንቱ ወይም አስታባበሪዉ ባለበት ብይን ይሰጥበታል።

ረ. አቤቱታ የቀረበበት ዳኛ ጉዳዩን እንዳያየው ብይን የተሰጠ እንደሆነ በሌላ ወይም በሌሎች ዳኞች እንዲታይ ይደረጋል።

4. በዚህ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 3 (ለ)፣ (ሐ) እና (መ) የሚሰጥ ብይን ማመልከቻው ከቀረበ በአስራ አምስት (15) ቀን ውስጥ መወሰን ያለበት ሲሆን ውሳኔው የመጨረሻ እና ይግባኝ የማይባልበት ይሆናል።

## ዓንቀፅ 11. አቤቱታው የሚያስከትለው ኪሳራ

በዚህ አዋጅ ዓንቀፅ 10 መሰረት ዳኛ ከችሎት እንዲነሳ የሚቀርበው አቤቱታ ፍርድ ቤቱ አግባብነት የለውም ብሎ ሳይቀበለው የቀረ እንደሆነ በሌላኛው ተካራካሪ ወገን ለደረሰው ኪሳራ ካለ ወዲያውኑ ወይም በዋናው ጉዳይ ከሚታየው ኪሳራ ጋር ተጠቃልሎ ሊወሰን ይችላል።

## ክፍል ሁለት
## የፍርድ ቤት አደረጃጀት

## ዓንቀፅ 12. የፍርድ ቤት እርከን (ደረጃ)

1. የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድ ቤቶች በህገ መንግስት እንደተደነገገ እንደየስልጣን ደረጃቸው ከላይ ወደ ታች ሲቀመጡ፤

ሀ. ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ፣

ለ. ማእኸላይ ቤት ፍርድን

ሐ. ወረዳ ቤት ፍርድን እዮም።

2. ኣብ ትሕቲ ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ክልል ትግራይ ፕረዚደንት፣ ምክትል ፕረዚደንት፣ ፣ ዳያኑ፣ ቤት ፅሕፈት ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ፣ መጋባእያታት፣ ዋና ሬጅስትራር፣ ክፍሊ ሬጅስትራር፣ ሓገዝቲ ዳያኑን ሰብ ሙያ ምርምር ሕግን፣ ደገፍቲ ከይዲ ስራሕን ሰራሕተኛታትን ይህልዉ።

3. ኣብ ትሕቲ ማእኸላይ ቤት ፍርዲ ፕረዚደንትን ምክትል ፕረዚደንትን፣ ቤት ፅሕፈት ማእኸላይ ቤት ፍርዲ ፣ ምድብ መጋባእያታት፣ መጋባእያታት፣ ዳያኑ፣ ክፍሊ ሬጂስትራር፣ ሬጅስትራር ደገፍቲ ከይዲ ስራሕን ሰራሕተኛታትን ይህልዉ።

4. ኣብ ትሕቲ ወረዳ ቤት ፍርዲ ፕረዚደንት፣ ምድብ መጋባእያታት፣ ዳያኑ፣ ሬጂስትራር፣ ደገፍቲ ከይዲ ስራሕትን ሰራሕተኛታትን ይህልዉ።

**ዓንቀፅ 13. <u>መጋባእያታት ቤት ፍርዲ</u>**

1. ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ፦

ሀ. መጋባእያ ዋኒን ፍትሃብሄር፣

ለ. መጋባእያ ዋኒን ገበን፣

ሐ .መጋባእያ ዋኒን ሰበርን ይህልዎ።

2. ፕረዚደንት ወይ ምክትል ፕረዚደንት ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ኣብ ዝኾነ መጋባእያ ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ኣካቢ ኮይኑ ክሰርሕ ይኽእል።

3. ማእኸላይ ወይ ወረዳ ቤት ፍርዲ፦

ሀ. መጋባእያ ዋኒን ፍትሃብሄርን

ሀ. ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፣

ለ. ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና

ሐ. የወረዳ ፍርድ ቤት ናቸው።

2 በጠቅላይ ፍርድ ቤት ስር ፕረዚዳንት፣ ምክትል ፕረዚዳንት፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፅሕፈት ቤት፣ ችሎቶች፣ ዋና ሬጅስትራር፣ የረጂስትራር ክፍል፣ ረዳት ዳኞች እና የህግ ምርምር ባለሙያዎች፣ ደጋፊ የስራ ሂደቶች እና ሰራተኞች ይኖራሉ።

3 በከፍተኛ ፍርድ ቤት ስር ፕረዚዳንትና ምክትል ፕረዚዳንት፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፅሕፈት ቤት፣ ምድብ ችሎቶች፣ ችሎቶች፣ ዳኞች፣ የረጂስትራር ክፍል፣ ሬጅስትራር፣ ደጋፊ የስራ ሂደቶች እና ሰራተኞች ይኖራሉ።

4 በወረዳ ፍርድ ቤት ስር ፕረዚዳንት፣ ምድብ ችሎቶች፣ ዳኞች፣ የረጂስትራር፣ ደጋፊ የስራ ሂደቶች እና ሰራቶኞች ይኖራሉ።

**<u>ዓንቀፅ 13. የፍርድ ቤት ችሎቶች</u>**

1. ጠቅላይ ፍርድ ቤት፡

ሀ. የፍትሃብሄር ጉዳይ ችሎት፣

ለ. የወንጀል ጉዳይ ችሎት እና፣

ሐ. የሰበር ጉዳይ ችሎት ይኖረዋል።

2 የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕረዚዳንት ወይም ምክትል ፕረዚዳንት በማንኛውም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎት ሰብሳቢ ሆኖ ሊሰራ ይችላል።

3 የከፍተኛ ወይም የወረዳ ፍርድ ቤት

ሀ. የፍሃትብሄር ጉዳይ ችሎት

ለ. መጋባእያ ዋኒን ገበንን ክህልዎ ይኽእል።

4. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1ን 3ን ዝተመልከተ እንተሃለወ'ውን ከም ኣድላይነቱ ዝተፈለዩ ዋኒናት ዝተኣናገድሉ ፍሉይ መጋባእያታት ክህልዉ ይኽእሉ።

5.ፕረዝደንት ወይ ምክትል ፕረዚደንት ማእኸላይ ቤት ፍርዲ ኣብ ዝኾነ መጋባእያ ማእኸላይ ቤት ፍርዲ ኣካቢ ኮይኑ ክሰርሕ ይኽእል።

6. ፕረዚደንት ወረዳ ቤት ፍርዲ ኣብ ዝኾነ መጋባእያ እቲ ቤት ፍርዲ ተሰይሙ ክሰርሕ ይኽእል።

**ክፍሊ- ሰለስተ**

**ዕላማ፣ ስልጣን ዳይነትን ኣሰራርሓ መጋባእያን**

**ዓንቀፅ 14. ሓፈሻዊ ዕላማ ቤት ፍርዲ**

ቤት ፍርዲ ዝስዕቡ ሓፈሻዊ ዕላማታት ይህልውዎ።

1.ኣብ ሃገራውን ክልላውን ሕገ መንግስቲ ዝተደንገጉ መሰላትን ነፃነትን ክኽበሩ ምግባር፤

2.ኣብ መንጎ ሰባት ዝለዓሉ ጎንፂ ብመሰረት ሕጊ ዕልባት ብምሃብ ምእላይ፤

3. ልዕልነት ሕጊ ብምርግጋፅ ንህንፀት ዲሞክራሲ፣ ሰላምን ልምዓትን ክልልና ኣበርክቶ ምግባር ይኸውን።

**ዓንቀፅ 15. ሓፈሻዊ ስልጣን ዳይነት ቤት ፍርዲ**

ቤት ፍርዲ ዝህልዎ ስልጣን ዳይነት ፦

1. ብሕገ መንግስቲ ወይ ብኻልእ ሕጊ ክልል ወይ ፌደራል ኣብ ዝተደንገገ ክልላዊ ዋኒን፤
2. ኣብ ትሕቲ ስልጣን ዳይነት ቤት ፍርዲ ፌደራል ዝሽፈን ኮይኑ ብውክልና ኣብ ዝረአ ዋኒን፤

ለ. የወንጀል ጉዳይ ችሎት ሊኖሩት ይችላል።

4 በዚህ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 እና 3 የተመለከው ቢኖርም እንደኣስፈላጊነቱ የተለዩ ጉዳዮች የሚያዩ ልዩ ችሎቶች ሊኖሩት ይችላሉ።

5 የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕረዚዳንት ወይም ምክትል ፕረዝዳንት በማንኛዉም የፍርድ ቤቱ ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ ሆኖ ሊሰራ ይችላል።

6 የወረዳ ፍርድ ቤት ፕረዚዳንት በማንኛውም የፍርድ ቤቱ ችሎት ተሰይሞ ሊሰራ ይችላል።

**ክፍል -ሶስት**

**አላማ፣ የዳኝነት ስልጣንና የችሎት ኣሰራር**

**ዓንቀፅ 14. የፍርድ ቤት አጠቃላይ አላማ**

ፍርድ ቤቱ የሚከተሉት አጠቃላይ ኣላማዎች ይኖሩታል።

1. በአገራዊ እና ክልልዊ ህገ-መንግስቶች የተደነገጉትን መብቶችና ነፃነቶች እንዲከበሩ ማደረግ፤
2. በሰዎች መካከል የሚነሱ ግጭቶች ሕግን መሰረት ያደረገ ውሳኔ በመስጠት መፍታት ፤
3. የህግ የበላይነት በማረጋገጥ በዚህ ክልል ለዴሞክራሲ፣ ለሰላም እና ለልማት ግንባታ አስተዋፅኦ ማድረግ ይሆናል።

**አንቀፅ 15. የፍርድ ቤት አጠቃላይ የዳኝነት ሥልጣን**

ፍርድ ቤት የሚኖረው የዳኝነት ስልጣን፦

1. በሕገ መንግስት ወይም በሌላ የክልሉ ወይም የፌደራል ሕግ በተደነገገ የክልል ጉዳዮች ላይ፣
2. በፌደራል ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን ስር የሚሸፈን ሆኖ በውክልና በሚታይ ጉዳይ ላይ፣

3. ዋኒናት ፍትሃብሄር ይኹን ገበን ብቀጥታ ክሲ ፣ ብይግባኣኒ ወይ ብሰበር ናይ ምርኣይ ስልጣን ይህልዎ።

**ዓንቀፅ 16. <u>ፈላማይ ብርኪ ስልጣን ዳይነት ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ</u>**

1.ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ኣብ ክሊ እዞም ዝስዕቡ ዋኒናት ፈላማይ ብርኪ ስልጣን ዳይነት ኣለዎ።

ሀ. ብመሰረት ሕገ መንግስቲ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ዓንቀፅ 80(2) ብውክልና ብቐጥታ ክሲ ዝተወሃቦ ዋኒን፤

ለ. ብመሰረት እዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝርእዮ ዋኒን ፌደራል ምስ ዋኒን ክልል ብምትሕውዋሱ ብሓደ ተጠሚሮም ክርኣዩ ዝግበኦምን ክፍላለዩ ዘይኽእሉን ዋኒንናት ኾይኑ እንትርከብ፤

ሐ. ኣብ ሕጊ ስነ-ስርዓት ብዝተደንገገ መሰረት ሓደ ዋኒን ካብ ሓደ ማእኸላይ ቤት ፍርዲ ናብ ካሊእ ማእኸላይ ቤት ፍርዲ ተዛዊሩ ክርአ ሕቶ እንትቐርበሉ ይኸውን።

2.ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ብቐጥታ ዝርእዮ ዝኾነ ዋኒን ብሰለስተ ዳያኑ ይኸውን።

**ዓንቀፅ 17. <u>ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ብይግባኣኒ ዝርእዮ ዋኒን</u>**

1. ማእኸላይ ቤት ፍርዲ ብፈላማይ ብርኪ ስልጣኑ ውሳነ ዝሃበሉ ዋኒን፤

2. ማእኸላይ ቤት ፍርዲ ብይግባኣኒ ርእዩ ካብ ወረዳ ቤት ፍርዲ ዝተለወጠ ውሳነ እንተሂቡ፤

3. በፍትሃብሄር ሆነ በወንጀል ጉዳይ ላይ በቀጥታ ክስ ወይም በይግባኝ ወይም በሰበር ሰሚ ችሎት የማየት ስልጣን ይኖረዋል።

**ዓንቀፅ 16. <u>የጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጀመርያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን</u>**

1. ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የመጀመርያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን አለው።

ሀ. በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ዓንቀፅ 80(2) መሰረት በውክልና በቀጥታ ክስ የማየት ስልጣን የተሰጠው ጉዳይ፤

ለ. በዚህ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 መሰረት የሚያየው የፌደራል ጉዳይ ከክልል ጉዳይ ጋር በመቀላቀሉ ምክንያት አንድ ላይ ተጣምረው ሊታዩ የሚገባቸው እና መነጣጣል እማይችሉ ሆኖ ሲገኝ፤

ሐ. በስነ-ስርዓት ሕግ በተደነገገው መሰረት አንድ ጉዳይ ከአንድ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተዛውሮ እንዲታይ ጥያቄ ሲቀርብለት ይሆናል።

2. ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቀጥታ የሚያየው ማንኛውም ጉዳይ በሦስት ዳኞች ይሆናል።

**ዓንቀፅ 17. <u>ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ የሚያየው ጉዳይ</u>**

1. ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመርያ ደረጃ ስልጣኑ ውሳኔ የሰጠበት ጉዳይ፤

2. ከፍተኛው ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ ከወረዳ ፍርድ ቤት የተለወጠ ውሳኔ የሰጠ እንደሆነ፤

3. ተኻታዕቲ ወገናት ክልቲኦም ይግባኣኒ ዝበልሎም ዋኒናት ብይግባኣኒ ሰማዒ ከይተጠመሩ ብምትራፎም ሓዲኡ ፀኒዑ እቲ ሓደ እንትልወጥ ንኽልቲኡ ብይግባኣኒ ናይ ምርኣይ ስልጣን፤

4. ብይግባኣኒ ንክርኢ ብካልኦት ሕግታት ስልጣን ዝተውሃቦ እንትኸውን ብይግበአኒ ናይ ምርኣይ ስልጣን ይህልዎ።

5. ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ብይግበአኒ ዝርእዮ ዋኒን ብሰለስተ ዳያኑ ይኸውን።

**ዓንቀፅ 18.ፓነል መጋባእያ**

1. ኣብዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 16 ንኡስ ዓንቀፅ 2ን ዓንቀፅ 17 ንኡስ ዓንቀፅ 6ን ዝተመልከተ እንተሃለወ'ውን ኣብ መንጎ መጋባእያታት ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ እቲ ሕጊ ኣብ ትርጉም ኣፈላላይ ዘስዕብ ወይ ዝተሓላለኸ ኾይኑ ንኣወሃህባ ፍትሒ ዘፀግም ነገር እንትጋጥም ፕረዚዳንት ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ብናይ ባዕሉ ተበግሶ ብዘቕርቦ ወይ ካብ መጋባእያታት ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ወይ ካብ መንጎ ተኻታዕቲ ወገናት ብዝቐርብ ሕቶ መሰረት ብሰለስተ ዳያኑ ክረአ ዝነበሮ ጉዳይ ካብ ሰበር መጋባእያ ብዝተፈለየ መልክዑ ሓሙሽተ ዳያኑ ተሰይሞም ክርእይዎ ይግበር።

2. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝተደንገገ ከምዘሎ ኮይኑ ኣብ ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ብፓነል መጋባእያ ተራእዩ ዝተወሰነ ዋኒን ብመጋባእያ ሰበር ንክርአ ጥርዓን እንተቐሪቡ ብሓሙሽተ ዳያኑ ተፃርዩ የቕርብ እንተተባሂሉ ብሸውዓተ ዳያኑ ተሰሚዑ ይውሰን።

3. ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ይግባኝ ያሉባቸው ጉዳዮች በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሳይጣመሩ በመቅረታቸው ምክንያት አንዱ ፀንቶ ሌላኛው ሲለወጥ ሁለቱንም በይግባኝ የማየት ስልጣን፤

4. በይግባኝ እንዲያይ በሌሎች ሕጎች ስልጣን የተሰጠው ሲሆን በይግባኝ የማየት ስልጣን ይኖረዋል።

5. ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ የሚያየው ጉዳይ በሦስት ዳኞች ይሆናል።

**ዓንቀፅ 18. የፓነል ችሎት**

1. በዚህ አዋጅ ዓንቀፅ 16 ንኡስ ዓንቀፅ 2 እና ዓንቀፅ 17 ንኡስ አንቀፅ 6 የተመለከተ ቢኖርም በጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎቶች የህግ ትርጉም ልዩነት ሲፈጠር ወይም የተወሳሰበ ሆኖ ለፍትህ አሰጣጥ አስቸጋሪ ሁኔታ ሲያጋጥም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕረዚዳንት በራሱ አነሳሽነት በሚያቀርበው ወይም በተከራካሪ ወገኖች በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት በሦስት ዳኞች ሊታይ ይገባው የነበረ ጉዳይ ከሰበር ችሎት በተለየ ሁኔታ አምስት ዳኞች ተሰይመው እንዲያዩት ይደረጋል።

2. በዚህ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በጠቅላይ ፍርድ ቤት የፓነል ችሎት ታይቶ የተወሰነ ጉዳይ በሰበር ችሎት እንዲታይ አቤቱታ የቀረበ እንደሆነ በአምስት ዳኞች ተጣርቶ፤ ያቀርባል የተባለ እንደሆነ በሰባት ዳኞች ተሰምቶ ይወሰናል።

ዓንቀፅ 19. ዕላማን ስልጣንን ሰበር መጋባእያ ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ

1. ኣብ ዓንቀፅ 14 እዚ እዋጅ ዝተመልከተ ሓፈሻዊ ዕላማ ኣብያተ ፍርዲ ከምዘሎ ኮይኑ ሰበር ሰማዒ መጋባእያ ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ሓፈሻዊ ረብሓ ህዝብን ህንፀት ስርዓት ዳይነትን መሰረት ዝገበሩ ዝስዕቡ ዕላማታት ይህልውዎ።

ሀ.ኣብ ስርዓት ዳይነት እዚ ክልል ንተመሳሳሊ ዋኒናት ተመሳሳሊ ዕልባት ክወሃብ ወይ ውፅእነት ኣተረጓጉማን ኣፈፃፅማን ሕጊ ክህሉ ምግባር፤

ለ. ብታሕተዋይ ቤት ፍርዲ ወይ ዳይነት ወሃቢ ኣካል ዝተፈፀመ መሰረታዊ ጌጋ ሕጊ ብምእራም ክትትልን ቁፅፅርን ምግባር ወይ፤

ሐ. ንምዕባለ ሕግን ስነ ሕግን እዚ ክልል ምስራሕ እዩ።

2. ሰበር ሰማዒ መጋባእያ ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ናይ መወዳእታ ዕልባት ኣብ ዝረኸበን መሰረታዊ ስሕተት ሕጊ ኣብ ዘለዎን ክልላዊ ዋኒን ክርኢ ስልጣን ዳይነት ዝህልዎ:-

ሀ.ኣብ ወረዳ ቤት ፍርዲ ተወሲኑ ብይግብኣኒ ኣብ ማእኸላይ ቤት ፍርዲ ተራእዩ ዝፀንዐ ክልላዊ ዋኒን፤

ለ. ኣብ ወረዳ ቤት ፍርዲ ተወሲኑ ኣብ ማእኸላይ ቤት ፍርዲ ብይግባኣኒ ዝተለወጠ ውሳነ ዝተውሃቦ ኮይኑ ብይግባኣኒ ዝቐረበሉ ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ናይ መወዳእታ ዕልባት ዝሃበሉ ክልላዊ ዋኒን፤

ሐ.ብኻልኦት ሕግታት ብዝተውሃቦ ስልጣን መሰረት ብይግባኣኒ ዝቐረበሉ ማእኸላይ

ዓንቀፅ 19. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አላማ እና ስልጣን

1. በዚህ አዋጅ ዓንቀፅ 14 የተመለከተውን የፍርድ ቤቶች አጠቃላይ አላማ እንደተጠበቀ ሆኖ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለአጠቃላይ የህዝብ ጥቅምና ለዳኝነት ስርዓት ግንባታ መሰረት ያደረጉ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል።

ሀ. በክልሉ የዳኝነት ስርአት ለተመሳሳይ ጉዳዮች ተመሳሳይ እልባት ለመስጠት ወይም ወጥነት ያለው የህግ አተረጓጎም እና አፈፃፀም እንዲኖር ለማድረግ፤

ለ. በስር ፍርድ ቤት ወይም ዳኝነት ሰጪ አካል የተፈፀመውን መሰረታዊ የህግ ስህተት በማረም ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ ወይም፤

ሐ. ለክልሉ ህግ እና ስነ-ህግ እድገት መስራት ነው።

2. የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የመጨረሻ እልባት ባገኘና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት የክልል ጉዳይ ላይ የመዳኘት ስልጣን የሚኖረው፦

ሀ. በወረዳ ፍርድ ቤት ተወስኖ በይግባኝ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የፀና የክልል ጉዳይ

ለ. በወረዳ ፍርድ ቤት ተወስኖ በይግባኝ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲለወጥና ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባይ አይቶ የመጨረሻ እልባት የሰጠበት የክልል ጉዳይ፤

ሐ. ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሌሎች ህጎች በተሰጠው ስልጣን መሰረት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ

ቤት ፍርዲ መዕለቢ ዝሃበሉ ክልላዊ ዋኒን፤

መ.ኣብ ማእኸላይ ቤት ፍርዲ ተወሲኑ ኣብ ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ብይግባኣኒ ተራእዩ ዕልባት ዝረኸበ ክልላዊ ዋኒን፤

ረ.ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ብኻልኦት ሕግታት ብዝተውሃቦ ስልጣን መሰረት ብይግባኣኒ ርእዩ ውሳነ ዝሃበሉ ክልላዊ ዋኒን፤

ሰ. ክልላዊ ስልጣን ዳይነት እንዳሃለወ ስልጣን ዳይነት ፌደራል እዩ ብምባል ወይ ስልጣን ዳይነት ፌዴራል እናሃለወ ስልጣን ዳይነት ክልል እዩ ብምባል ኣብ ማእኸላይ ወይ ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ተራእዩ ናይ መወዳእታ ዕልባት ዝረኸበ ዋኒን፤

**ዓንቀፅ 20፡- <u>መገደዳይነት ውሳነ ሰበር መጋባእያ ክልል ትግራይ</u>**

1. ኣብ መንጎ ኣብያተ ፍርዲ ክልል ትግራይ ዝርአ ፍልሊ ኣተረጓጉማ ሕጊ ወይ ዝተሓላለኸ ኾይኑ ንኣወሃህባ ፍትሒ ዘፀግም ነገር እንተጋጥምን ብፕረዚዳንት ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ብናይ ባዕሉ ተበግሶ ወይ ሰበር ሰማዒ መጋባእያ ኣድላይነቱ እንተኣምነሉ ሕቶ ንፕረዚደንት እንተቐርብ ሸውዓተ ዳያኑ ኣብ ዝተሰየምሉ ብጭብጥነት ሒዙ ኣብ ክልላዊ ዋኒን ዝህቦ ናይ ሕጊ ትርጉም ኣብ ተመሳሳሊ ዋኒን ኣብ ልዕሊ ኩሎም ብርኪ ኣብያተ ፍርዲ መገደዳይነት ውፅኢት ይህልዎ።
2. ሰበር ሰማዒ ዝህቦ ትርጉም ሕጊ መገደዳይ ዝኸውን ብዝተፈላለዩ መንገድታት ወይ ብሕትመት ንኹሉ ብርኪ ቤት ፍርዲ እንትግለፅ ይኸውን።
3. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝተደንገገ

እልባት የሰጠበት የክልል ጉዳይ፤

መ. በከፍተኛ ፍርድ ቤት ተወስኖ በጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ታይቶ እልባት ያገኘ የክልል ጉዳይ፤

ረ. ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በሌሎች ህጎች በተሰጠው ስልጣን መሰረት አይቶ ውሳኔ በሰጠበት ጉዳይ፤

ሰ. የክልል የዳኝነት ስልጣን ሆኖ እያለ የፌደራል የዳኝነት ስልጣን ነው በማለት ወይም የፌዴራል የዳኝነት ስልጣን እያለ የክልል የዳኝነት ስልጣን ነው በማለት በከለለ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ጠቅላይ ፍርድ ቤት ታይቶ የመጨረሻ እልባት ያገኘ ጉዳይ፤

**ዓንቀፅ 20፡-<u>የትግራይ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ አስገዳጅነት</u>**

1. በትግራይ ፍርድ ቤቶች መካከል ያለው የህግ ትርጉም የተለያየ በመሆኑ ወይም ከውስብስብነቱ የተነሳ ለፍትህ አሰጣጥ አዳጋች ሲሆን ፕረዝዳንት በራሱ ተነሳሽነት በሚያቀርበው ወይም ሰበር ሰሚ ችሎት አስፈላጊነቱ ሲያምንበትና ለፕረዝደንት ጥያቄ ሲቀርብ ሰባት ዳኞች በተሰየሙበት በጭብጥነት ይዞ በክልላዊ ጉዳይ በሚሰጠው የህግ ትርጉም በሁሉም ፍርድቤቶች በተመሳሳይ የህግ ጭብጥ የአስገዳጅነት ውጤት ይኖረዋል።
2. በዚህ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጠው ውሳኔ በሁሉም የፍርድ ቤት እርከን አስገዳጅነት የሚኖረው በልዩ ልዩ መንገድ ለፍርድ ቤቶች ሲገለፅ ወይም ሲታተም ይሆናል።

እንተሃለወ እኳ ሰበር ሰማዒ መጋባእያ ኣቐዲሙ ዝሃቦ መገደዳይ ትርጉም ንምልዋጥ ዘኽእሎ ብቑዕ ምኽንያት እንተተረኺቡ ትሽዓተ ዳያኑ ብዝተሰየምሉ መጋባእያ ኣብ ተመሳሳሊ ጭብጢ ዝተፈለየ መገደዲ ትርጉም ክህብ ይኽእል፣

## ዓንቀፅ 21 መሰረታዊ ስሕተት ሕጊ

1.ሓደ ናይ መወዳእታ ዕልባት ዝረኸበ ክልላዊ ዋኒን መሰረታዊ ስሕተት ሕጊ ተፈፂምዎ ንምባል ዝርኣየሉ መነፅር፡-

ሀ. ንመሰረታውን ስነ ስርዓታውን መትከላት ሕጊ ብምጥሓስ ወይ ብምግዳፍ ዝተወሃበ ውሳነ ኮይኑ ኣብ ልዕሊ መሰል ደቂ ሰባት ወይ ኣብ ሓፈሻዊ ስርዓት ፍትሒ ኣሉታዊ ፅዕንቶ ዘሕድር እንተኾይኑ ፤ወይ

ለ. እቲ ጥርዓን ዝቐረቦ ውሳነ ብውሳነታት ሰበር ፌደራልን ክልልን ቅቡል ንዝተገበሩን ዝማዕበሉን መትከላት ሕጊ ዝጓነፅ ኮይኑ እንትርከብ ወይ፤

ሐ.ካብ ስልጣን ዳይነት ወፃኢ ምድናይ ወይ ኣብ ክሊ ስልጣን ዝወድቕ ዋኒን ዘይምድናይ ፤ወይ

መ. ንመትከላት ነፃነትን ስነ-ምግባርን ዳይነት ብምጥሓስ ዝተወሰነ ውሳነ እንተኾይኑ፤ ወይ

ሰ.ዉሳነ ዘይዓረፎ ዋኒን ምፍፃም ወይ ፤ ዝተወሰነ ውሳነ ዘይምፍፃም፤

ሸ.ክውስድ ዝግብኦ ናይ ሕጊ ግምት ዘይምውሳድ ወይ ክውሰድ ዘይግብኦ ግምት ምውሳድ/ብሕጊ ዘይኮነስ ብሕሊና ምውሳን፤ ወይ

ቀ. ንዝቐረበ ቀዳማይ ብርኪ መቃወምያ ብይን ከይሃካ ምሕላፍን ዝኣመሰሉ እዮም።

2.ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝተመልከተ እንተሃለወ'ውን፡-

3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ ዓንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም ሰበር ሰሚ ችሎት አስቀድሞ የሰጠውን አስገዳጅ ትርጉም ለመለወጥ ብቁ ምክንያት ሲገኝ ዘጠኝ ዳኞች በተሰየሙበት በተመሳሳይ ጭብጥ የተለየ አስገዳጅ ትርጉም ሊሰጥ ይችላል።

## ዓንቀፅ 21. መሰረታዊ የህግ ስህተት

1. አንድ የመጨረሻ እልባት ያገኘ ክልላዊ ጉዳይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል ለማለት የሚታይበት መነፅር፦

ሀ. መሰረታዊ እና ስነ-ስርአታዊ የህግ መርሆችን በመጣስ ወይም በመተላለፍ የተሰጠ ውሳኔ እና በሰዎች መብት ላይ ወይም በፍትህ ስርዓቱ ላይ አላስፈላጊ ተጽዕኖ አስከትሎ ከሆነ ፤ ወይም

ለ. አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በፌደራል እና ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀባይነት ያገኙና የዳበሩ የህግ መርሆችን የሚፃረር ሆኖ ሲገኝ ወይም፤

ሐ. ከዳኝነት ስልጣን ውጭ መዳኘት ወይም በስልጣን ስር የሚወድቅ ጉዳይን አለመዳኘት፤

መ. የዳኝነት ነፃነትንና የዳኝነት ስነ-ምግባር መርሆችን በመጣስ የተወሰነ ውሳኔ ሲሆን ወይም፤

ሰ. ፍርድ ያላረፈበት ጉዳይን ማስፈፀም፤ የተወሰነውን ውሳኔ አለመፈፀም ወይም፤

ሸ. ሊወሰድ የሚገባውን የህግ ግምት አለመውሰድ ወይም ሊወሰድ የማይገባውን የህግ ግምት መውሰድ/ በህግ ሳይሆን በህሊና መወሰን ወይም፤

ቀ. ለቀረበ የመጀመርያ ደረጃ መቃወሚያ ብይን ሳይሰጥባቸው ማለፍ እና የመሳሰሉትን ናቸው።

2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 የተመለከተውን ቢኖርም፦

ሀ. ካብ ሕግታት ቤተሰብን መሰርሕን ሰራሕተኛን ወፃኢ ክሳብ ብር 10,000 (ዓሰርተ ሽሕ ) ዝበፅሕ ናይ ፍትሃብሄር ክትዕ፤

ለ. ዋኒን ደንቢ ምትሕልላፍ፤

ሐ. ኣብ ካልእ ሕጊ ብግልፂ ተዘይተመልኪቱ ብዝኾነ ብርኪ ቤት ፍርዲ ዘይሓለፈ ናይ መወዳእታ ምምሕዳራዊ ውሳነ ዝተወሃበሉ ምምሕዳራዊ ዋኒን ናብ ሰበር መጋባእያ ኣይቐርብን።

**ዓንቀፅ 22. <u>ኣቀራርባ ጥርዓን ሰበርን ስነ-ስርዓቱን</u>**

1. ዋኒኑ ብሰበር ክረኣየሉ ጥርዓን ዘቕርብ ኣመልካቲ ሰበር፦

ሀ. ውሳነ ታሕተዋይ ቤት ፍርዲ መሰረታዊ ስሕተት ሕጊ ተፈፂምዎ ዝብለሉ ምኽንያት ኣብ መመልከቲ ጥርዓኑ ሓፂርን ግልፅን ብዝኾነ ኣገባብ የቕርብ።

ለ. ምስቲ ዘቕረቦ መመልከቲ ጥርዓን ናይ'ቲ ዝጠርዐሉ ውሳነን ናይ ታሕተዋይ ቤት ፍርዲ ውሳነን ብእኹል ቕዳሕ ኣተሓሒዙ የቕርብ።

ሐ. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 (ለ) ዝተደንገገ ከምዘሎ ኮይኑ ሰበር ሰማዒ መጋባእያ ኣድላይ ኮይኑ እንተረኺብዎ እቲ ዋና መዝገብ ወይ ቅዳሑ ክቐርበሉ ክእዝዝ ይኽእል ።

2. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝተደንገገ ሕልው ኮይኑ ዝኾነ ውሳነ ቤት ፍርዲ መሰረታዊ ስሕተት ሕጊ ዘለዎ ኾይኑ ወይ ምዝባዕ ልዕልና ሕጊ ዘብፀሐ እንዳሃለወ ብእዋኑ ኣብ ሰበር ወይ ይግባኣኒ ሰማዒ ቤት ፍርዲ ብብቑዕ ምኽንያት ከይቀረበ ብምትራፉ ግጉይ ውሳነ ፀኒዑ ንከይነብር ብመመልከቲ ሕቶ እንትቐርበሉን ፕረዚደንት

ሀ. ከቤተሰብ እና ከአሰሪና ሰራተኛ ሕጎች ውጭ እስከ ብር 10,000 (አስር ሺ) የሚደርስ የፍትሃብሄር ክርክር ፤

ለ. ጉዳዩ የደንብ መተላለፍ ሲሆን ፤

ሐ. በሌላ ሕግ በግልፅ ካልተደነገገ በስተቀር በማናቸውም ደረጃ ፍርድ ቤት ያልታየ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠበት አስተዳደራዊ ጉዳይ ለሰበር ችሎት አይቀርብም።

**<u>ዓንቀፅ 22. የሰበር አቤቱታ አቀራረብና ስነ-ስርዓቱ</u>**

1. ጉዳዩ በሰበር እንዲታይለት አቤቱታ የሚያቀርብ የሰበር አመልካች፦

ሀ. የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል የሚልበትን ምክንያት በአቤቱታ ማመልከቻው ላይ በአጭሩና ግልፅ በሆነ አኳኃን ያቀርባል።

ለ. ከሚያቀርበው የአቤቱታ ማመልከቻ ጋር አቤቱታ ያቀረበበትን የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በበቂ ቅጂ አያይዞ ያቀርባል።

ሐ. በዚሁ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 (ለ) የተደነገገው እንዳለ ሆኖ የሰበር ሰሚ ችሎት አስፈላጊ ሆና ያገኘው እንደሆነ ዋናው መዝገብ ወይም ቅጂው እንዲቀርብለት ሊያዝ ይችላል።

2. በዚህ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ወይም የሕግ የበላይነት መዘባት ያደረሰ ሆኖ ሳለ በተከራካሪ ወገኖች የሰበር አቤቱታ ወደ ሰበር ችሎት ወይም የይግባኝ አቤቱታ ወደ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሳይቀርብ በመቅረቱ የተሳሳተው ውሳኔ ፀንቶ እንዳይኖር ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕረዚዳንት ማመልከቻ ቀርቦ

እንትኣምነሉን ናብ ሰበር ሰማዒ መጋባእያ ክቐርብ ይኽእል።

3. ብመሰረት እዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 2 ዝወሃብ ውሳነ ኣብ ልዕሊ ኣብ ታሕተዋይ ቤት ፍርዲ ይካተዑ ንዝነበሩ ውልቀሰባት መሰልን ግቡእን ፅልዋ ዘሕድር እንተኾይኑ እቶም ተኻታዕቲ ወገናት ተፀዊዖም ሓሳብ ወይ መልሲ ክህብሉ ይኽእሉ።

4.ናይ'ዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 2ን 3ን መሰረት ብምግባር ዝውሰን ዋኒን ገበን ኣብ ልዕሊ ተፀዋዒ ውልቀሰብ ኣወንታዊ ውፅኢት እንተህልዎን ዝጠቕሞ እንተኾውንን ጥራሕ ይኸውን።

5.ዝኾነ ናይ መወዳእታ ውሳነ ዝረኸበ ክልላዊ ዋኒን ናብ ሰበር ሰማዒ መጋባእያ እንትቐርብ ሰለስተ ዳያኑ ብዝተሰየምሉ መጋባእያ እቲ ጥርዓን ተመርሚሩ ናብ ሰበር መጋባእያ ክቐርብ ይግባእ ተባሂሉ እንትእዘዝ ይኸውን።

6.ኣብዚ ኣዋጅ ዓንቀፅ 20 ዝተደንገገ በዝሒ ዝስየሙ ዳያኑ ዝተመልከተ ከምዘሎ ኮይኑ መሰረታዊ ጌጋ ሕጊ ኣለዎ ተባሂሉ የቕርብ ዝተብሃለ ዋኒን ብሓሙሽተ ዳያኑ ተሰሚዑ ዕልባት ክረክብ ይግበር።

7. ጥርዓን ሰበር ክቐርብ ዝኽእል ናይ መወዳእታ ውሳነ ካብ ዝተወሃበሉ ዕለት ጀሚሩ ኣብ ውሽጢ 60 /ስልሳ/ መዓልቲ ይኸውን።

8. ኣብዚ ኣዋጅ ዝተደንገጉ ከምዘለዉ ኮይኖም ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ ሰበር ሰማዒ መጋባእያ ዝምርሓሉ ስነ ስርዓት ዝድንግግ መምርሒ ከውፅእ ይኽእል።

ሲታመነበት ወደ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ ይቻላል፡፡

3. በዚህ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 2 የሚሰጠውን ውሳኔ በስር ፍርድ ቤት ሲከራከሩ የነበሩትን ግለሰቦች መብት እና ግዴታ ላይ ተፅእኖ ካለው ተከራካሪዎቹ ተጠርተው እንደየሁኔታው ሃሳብ ወይም መልስ ሊሰጡበት ይችላሉ፡፡

4.የዚህ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 2 ና 3 መሰረት በማድረግ የሚወሰነውን የወንጀል ጉዳይ በተጠሪው ግለሰብ ላይ አወንታዊ ውጤት የሚኖረውና የሚጠቅመው ሲሆን ብቻ ይሆናል፡፡

5 አንድ የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር ችሎት መታየት የሚችለው አስቀድሞ ሶስት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት የቀረበውን አቤቱታ ተመርምሮ ውሳኔው ለሰበር መቅረብ ይገባዋል ተብሎ ትእዛዝ ሲሰጥ ይሆናል።

6. በዚህ አዋጅ ዓንቀፅ 20 የተደነገገውን የዳኞች ስያሜ ብዛት እንዳለ ሆኖ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት ተብሎ ያቀርባል የተባለ ደግሞ በአምስት ዳኞች ተሰምቶ እልባት እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡

7. የሰበር አቤቱታ መቅረብ የሚችለው የመጨረሻ ውሳኔ ከተሰጠበት ዕለት ጀምሮ በ60 /ስድሳ/ ቀናት ውስጥ ይሆናል።

8. በዚህ አዋጅ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚመራበትን ስነ-ስርአት የሚደነግግ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**ዓንቀፅ 23. ፈላሚ ብርኪ ስልጣን ዳይነት ማእኸላይ ቤት ፍርዲ**

1. ማእኸላይ ቤት ፍርዲ ኣብ ልዕሊ እዞም ዝስዕቡ ክልላዊ ዋኒናት ፈላማይ ብርኪ ስልጣን ዳይነት ይህልዎ።

ሀ. ግምቱ ልዕሊ ብር 3,000,000.00 (ሰለስተ ሚልዮን ) ዝኾነ ዝንቀሳቀስ ንብረት፣

ዘይንቀሳቐስ ንብረት ወይ ድማ ዝንቀሳቐስን ዘይንቀሳቐስን ንብረት ኣብ ሓደ ክሲ ተደሚሮም ብምቕራብ ዝምስረቱ ክስታት ፍታብሄር ዝምልከት፤

ለ.ቅፅዓቱ ልዕሊ 15 ዓመት ፅኑዕ ማእሰርቲ ፣ ዕድመ ልክዕ ወይ ሞት ኣብ ዝኾነ ክልላዊ ዋኒን ገበን፣

ሐ. ብመሰረት ሕገ መንግስቲ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ዓንቀፅ 80 (4) ብውክልና ኣብ ዝተውሃቦ ዋኒን፤

መ. ኣብ ልዕሊ ኩሎም ክልላዊ ዋኒናት ግዕዝይናን ክልላዊ ሕገ-መንግስቲ ዝፃባእ ክልል ተንከፍ ዋኒን ገበንን፤

ረ. ዝኾነ በዓል መዚ ብምኽንያት ሓላፍነት ስርሑ ተሓታቲ ኣብ ዝኾኖ ዋኒን ገበን፤

ሰ. ኣብ ስራሕ ብዘለው ካልኦት ሕግታት ስልጣኑ ንማእኸላይ ቤት ፍርዲ ኣብ ዝተውሃበ ዋኒን ገበን ብቐጥታ ክሲ ናይ ምርኣይ ስልጣን፤

ሸ. ሓደ ዋኒን ካብ ሓደ ወረዳ ቤት ፍርዲ ናብ ካልእ ወረዳ ቤት ፍርዲ ወይ ናብ ማእኸላይ ቤት ፍርዲ ተዛዊሩ ክረአ ሕቶ እንትቐርበሉ ይኸውን።

2. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ (1) (ሀ) ዝተደንገገ

**ዓንቀፅ 23. የከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመርያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን**

1. ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚከተሉት የክልል ጉዳዩች ላይ የመጀመርያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል።

ሀ. ግምቱ ከብር 3,000,000 (ሦስት ሚልዮን ) በላይ የሆነ የሚንቀሳቀስ ንብረት፣ የማይንቀሳቀስ

ንብረት ወይም የሚንቀሳቀስ እና የማይቀሳቀስ ንብረት ተደምረው አንድ ላይ የሚቀርቡ የፍትሃብሄር ክሶች በሚመለከት፤

ለ. ቅጣቱ ከ15 ዓመት ፅኑ እስራት በላይ፣ ዕድሜ ልክ ወይም ሞት በሚያስቀጣ በማንኛውም ክልላዊ የወንጀል ጉዳይ ላይ፤

ሐ. በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ዓንቀፅ 80(4) መሰረት በውክልና በተሰጠው ጉዳይ ላይ፤

መ. በሁሉም የክልል የሙስና ወንጀል ጉዳዮችና የክልሉን ሕገ-መንግስት የሚጥስ ክልላዊ የወንጀል ነክ ጉዳይ ላይ፤

ረ. ማንኛውም ባለስልጣን በስራ ሃላፊነቱ ምክንያት ተጠያቂ በሚሆንበት የወንጀል ጉዳይ፤

ሰ. በስራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ስልጣኑ ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተሰጠ የወንጀል ጉዳይ ላይ በቀጥታ ክስ የማየት ስልጣን፤

ሸ. አንድ ጉዳይ ከአንድ ወረዳ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ ወረዳ ፍርድ ቤት ወይም ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተዛውሮ እንዲታይ ጥያቄ ሲቀርብለት ይሆናል።

2. በዚህ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ (1) (ሀ) የተደነገገው ቢኖርም አንድ የፌደራል ጉዳይ

እንተሃለወ እውን ሓደ ናይ ፌደራል ዋኒን ኣብ እዋን ኣፈፃፅማ ፍርዲ ብዝተፈላለየ ምኽንያት መጠን ገንዘቡ ካብቲ ንቀዳማይ ብርኪ ቤት ፍርዲ ፌደራል ዝተወሃበ ስረ ነገራዊ ስልጣን በሊፁ እንተረኸበ እኳ ከፈፅም ስልጣን ይህልዎ፡

3. ቀጥታ ክሲ ንምርኣይ ኣብ መጋባእያ ዝስየሙ በዝሒ ዳያኑ፦

ሀ. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 (ሀ) ፣ (ለ) ፣(ሐ) ፣ (መ)ን (ረ)ን ዝተደንገጉን ብውክልና ዝርእዮም ኩሎም ዋኒናት ገበን ፌደራል ሰለስተ ዳያኑ ኣብ ዝተሰየመሉ መጋባእያ ይርአዩ።

ለ. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 (ሐ) ዝተመልከተ ዋኒን ፍትሃብሄር እንተኾይኑ ብካሊእ ሕጊ ብሰለስተ ዳያኑ ክርአ ክሳብ ዘይተደንገገ ሓደ ዳይና ኣብ ዝተሰየመሉ መጋባእያ ይርአ።

ሐ.ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 3 (ለ) ዝተደንገገ እንተሃለወ እውን እቲ ቤት ፍርዲ ዝተሓላለኸ እዩ ኢሉ ንዝኣመነሉ ዋኒን ፍትሃብሄር ብመልዐላይነት ፕረዚደንት ማእኸላይ ቤት ፍርዲ ወይ ነቲ ዋኒን ብዝሓዘ ዳይና ሓታቲነት ብውሳነ ፕረዚደንትን ማእኸላይ ቤት ፍርድ ብሰለስተ ዳያኑ ክርእይ ይኽእል እዩ።

## ዓንቀፅ 24. ማእኸላይ ቤት ፍርዲ ብይግባኣኒ ዝርእዮም ዋኒናት

1. ማእኸላይ ቤት ፍርዲ ብይግበኣኒ ዝርእዮም ዋኒናት:-

ሀ. ወረዳ ቤት ፍርዲ ብፈላማይ ብርኪ ስልጣኑ ውሳነ ዝሃበሉ ዋኒን፤

ለ. ወረዳ ቤት ፍርዲ ካብ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ብይግባኣኒ ቐሪብሉ ዝተለወጠ ውሳነ ዝሃበሉ ዋኒን፤

በፍርድ አፈፃፀም ጊዜ በተለያየ ምክንያት የገንዘብ መጠኑ ለፌደራል መጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከተሰጠውን ስልጣን በልጦ ቢያገኘውም እንኳ የማስፈፀም ስልጣን ይኖረዋል።

3. በቀጥታ ክስ ለማየት በችሎት የሚሰየሙ የዳኞች ብዛት፡-

